የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፮ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 27
ADDIS ABABA-5th February ,2004


**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፪/፲፱፻፺፮ ዓ.ም


ከየመን ሪፐብሊክ ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........ ገጽ ፪ሺ፭፻፹፫


**CONTENTS**

Proclamation No. 392/2004


The Republic of Yemen Bilateral Air Services Agreement Ratification Proclamation ... Page 2583


## አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፪/፲፱፻፺፮

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በየመን ሪፐብሊክ መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የአየር አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በየመን ሪፐብሊክ መካከል እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር ፮ ቀን ፪ሺ በአዲስ አበባ ላይ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በየሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቶቻቸው መሠረት በተዋዋዮቹ ሀገሮች መጽደቁን የሚያረጋግጡ የዲፕሎማቲክ ሰነዶች ልውውጥ ከሚደረግበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO.392/2004.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE BILATERAL AIR SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF YEMEN

**WHEREAS,** a Bilateral Air Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Yemen, was signed in Addis Ababa, on the 6th day of September, 2000;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force after the exchange of notes confirming its ratification in compliance with the respective legal procedures in force in each country;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Said Agreement at its session on the 5th February, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**
ይህ አዋጅ "ከየመን ሪፐብሊክ ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፪/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **<u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በየመን ሪፐብሊክ መካከል እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር ፮ ቀን ፪ሺ በአዲስ አበባ ላይ የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት ፀድቋል።

፫. **<u>የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ሥልጣን</u>**

የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

1. **Short Title**
This Proclamation may be cited as "The Republic of Yemen Bilateral Air Services Agreement Ratification Proclamation No. 392/2004."

2. **Ratification of the Agreement**
The Bilateral Air Services Agreement Signed in Addis Ababa on the 6th day of September, 2000 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Yemen is hereby ratified.

3. **Power of the Minister of Infrastructure**

The Minister of Infrastructure is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the 5th day of February, 2004

**Done at Addis Ababa, this 5th day of February, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት